# ትግላችን




ሚያዝያ – ሀምሌ 1962
ቁጥር 3

# ትግላችን

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር
ወርሃዊ መፅሔት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

አዘጋጅ፡- ሃይሌ ፊዳ
c/o P. O. BOX 3198
10364 Stockholm 3
SWEDEN

ሚያዝያ – ሀምሌ 1962
ቁጥር 3 -

ዋጋው፡- 1 ብር

| | |
|---|---|
| የጎሣ ልዩነት? | 1 |
| የመንግሥቱን ጋዜጣ ስናገላብጥ | 8 |
| ሀ. እኛና ብሔራዊ ስሜት | 8 |
| ለ. ሺህ ቢታሰብ ያው በገሌ | 16 |
| የዓለም ጋዜጦች ስለኢትዮጵያ ምን ይላሉ? | 19 |
| ያገር ቤት ዜና | 23 |
| ሀ. የሠራተኞች ትግል | 23 |
| ለ. አልቲቶ ቀጥሎከል | 23 |
| ሐ. የትምህርት ችግር | 25 |
| ኢምፔሪያሊዝም በደቡብ ምሥራቅ እስያ | 27 |
| ግጥሞች | 37 |
| ሀ. ለሌኒን | 37 |
| ለ. ዘለዓለም ወጣት፡ዘለዓለም አስ ተማሪ | 41 |
| ሐ. ቅኔ | 40 |

ተከታታይ ዘመናት ውስጥ ... የሕዝቡ የዓመት የነፍስ ወከ
ፍ ገቢ በፕላኑ ዘመን ፍጻሜ ላይ 200 ብር ይደርሳል::
ገራም ነው፤፤ግን እኮ የሃያ ዓመት ፕላናችሁ ፍጻሜ ላይ
በተስፋ ጠብቅ የምትሉን ይኸ ሁለት መቶ ብር ዛሬ በአብዛ
ኛዎቹ የአፍሪካ አገሮች ታልፏ የሔደች የገቢ ልክ ናት::
የተሰጠንን ተስፋ "ጪቀ" ሁነን ከጠበቅን ከብዙ ዓመታት
በኋላ ዛሬ የአፍሪካ አገሮች ያሉበት ደረጃ እንደርሳለን
ማለት ነው::በጭራ የሚሰጣ ቢገኝ ጭቆናቸውን፤ድንቁርናችን
ን፤ድህነታችንን፤ባርነታችንንከኛም አልፈው ለሚመጡ የኢት
ዮጵያ ትውልዱ "በፕላናቸው" አጥንተው አስቀምጠውልናል ማለ
ት ነው::

እኛ በኢትዮጵያ ሕዝብ እስበዚህ ተስፋ አልቆረጥንም::ከተ
ውተበ ተበበት የጭቆናና የድንቁርና በነበሰት ቢፍታታ እስተ
ዋጭ ጠንከረው የኢትዮጵያ ሕዝብ "በዕድገት ፕላናችሁ" የ
ዘረጋችሁለትን ጭልምልም ያለ የጥፋት መንገድ ተወጥቶ በአ
ንድነት የኢትዮጵያዊ ሁሉ አለኘታ የሆነች ሀብታም ኢትዮጵ
ያ ይመሠርታል ብለን ዕምነት አለን::

ይህም የጉዳና ነጻነት ለሚጠይቀው ትግልና መሥዋዕትነት ተ
በናዴቶ ታታሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከተደቀነው ጃንንነቱና
ቋሬጥነቱ በይቆጠብ ጭቆናን ሊቷቷም መነሳቱ ለነገዪቱ ሕዝብ
ዊት ኢትዮጵያችን የማያወላውል ዋስትና ይሰጠናል::

<u>ማሳሰቢያ</u>

ይህ ጽሑፍ ከደረሰን በርከት ያሉ ወራት አልፈዋል::እስከ
ሁን ያላወጣነው በታና ጊዜ በጣነሱ መሆኑን ለአንባቢዎች
ስናስታውስ መዘግየቱ ደገም የሚሰጠውን ትምህርት በምንም
እንዳልቀነስው እያሰሰብን ነው::